## 1. ትርጉም

መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ቃል በቃል ሲፈታ ልዩ፣ ንጹሕ፣ የከበረ መጽሐፍ ማለት ነው።

ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ በቀለምና በብራና (በወረቀት) የተጻፈ፡ ከሌሎች ዓለማውያን መጻሕፍት የተለየና የከበረ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ነው (ሮሜ፤10፤17) ።

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር መጽሐፍ በመባል ይጠራል (ኢሳ፤ 34:16፣ ራዕ፤ 1:11)::

## 2. የመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭ

"... ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።" (2ጴጥ፤1፡21) ተብሎ እንደተመሰከረለት በመጽሐፍ ቅዱስ ለሚገኘው ቃል ምንጩ ራሱ ባለቤቱ ልዑል እግዚአብሔር ነው።

ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን የእግዚአብሔር እስትንፋስ በማለት ይጠሯቸዋል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ የሚሰጡ ቅዱሳት (የተለዩ፣ የተከበሩ) መጻሕፍት ናቸውና (2ጢሞ፤ 3፤15-17) ።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የቃሉ ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ቅዱስ መንፈሱን ያሳደረባቸው፣ ምሥጢሩንም የገለጠላቸው፣ በባለሟልነት የመረጣቸው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ (እየተነዱ) የጻፉት ቅዱስ መጽሐፍ ነው (ሉቃ፤1:1-4፤ 2ጴጥ፤1:21)::

## 3. የመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ

መጽሐፍ ቅዱስ ከ 4500 (ከክ.ል.በ.) — 100 (ዓ.ም.) ወደ 4600 ዓመታት በሚጠጋ ጊዜ ውስጥ ከ 40 በላይ በሚሆኑ ቅዱሳን ሰዎች እንደተጻፈ ይታመናል::

ብሉይ ኪዳንን ከአበው ሔኖክ እና ኢዮብ፣ ከሙሴ - ሳሙኤል የተነሱ የእስራኤል መሳፍንት፣ ከነገሥታት ዳዊት፣ ሰሎሞን፣ ምናሴ፤ ከነቢያት ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤልና ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ ዘመን የተነሱ ደቂቀ ነቢያት፤ እንዲሁም የእስራኤልን ነገሥታት ዜና መዋዕል የጻፉ ፀሓፍተ-እስራኤል ጽፈውታል።

ሐዲስ ኪዳንን የጻፉት ከሐዋርያት ማቴዎስ፣ ዮሐንስ (ወንጌላዊ)፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ (ወልደ እልፍዮስ)፣ ከ 72 አርድዕት ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ይሁዳ (የያዕቆብ ወንድም) እና ቅዱስ ጳውሎስ ናቸው::

በመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቃለሉ መጻሕፍት በተለያዩ ሰዎች፣ በተለያዩ ዘመናት የተጻፉ በመሆናቸው ምክንያት የተጻፉባቸው ቦታዎችና የተጻፉላቸው ሰዎችም እንዲሁ የተለያዩ ናቸው:: ይኸውም ኦሪት በስደት በግብጽና በከነዓን መካከል፣ መጻሕፍተ ኤርምያስ በምርኮ በፋርስ በባቢሎን፣ የመሳፍንት እና የነገሥት መጻሕፍት አብዛኛዎቹ በእስራኤል፣ ወንጌል በእስራኤልና በአካባቢዋ፣ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በሮም፣ በግሪክና በአካባቢው፣ እንደተጻፉ ይታመናል::

ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዳሁኑ የመጽሐፍ ቅርጽ ከመያዙ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጽሐፍ በብራና፣ በፓፒረስ (ከደንገል በሚሠራ ወረቀት) ተጽፎ በጥቅልል (Scroll) መልክ በኩምራን ዋሻ፣ በሙት ባሕር፣በሲና በረሐ፣ በእስክንድርያ፣ ጥንታውያን ቅጅዎቻቸው ተሰብስቦ በቀኖና ቤተክርስቲያን በ369 ዓ.ም. ቀርጠግና (ካርቴጅ) በተባለ ቦታ በተደረገ ጉባኤ በአንድ ጥራዝ መጽሐፍ ቅዱስ ተባለ። "<u>መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ብዙ መጻሕፍትን የያዘ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ነው"</u> የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው።

### *የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋዎች*

ለመጀመሪያ ጊዜ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በፅርዕ (ግሪክ) እና አራማይክ ተጽፈዋል:: ከነዚህ በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍ (ብሉያትና ሐዲሳት) በሙሉም ሆነ በከፊል የተተረጐሙባቸው ሌሎች ጥንታውያን ቋንቋዎች መካከል ሱርስት (Syriac) ፣ ግእዝ (Ethiopic) ፣ ሮማይስጥ (Latin) ፣ ዮናኒ (Public Greek) በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው::

ከዚህ በኋላ ግን ቅዱሳን ሐዋርያት በመላው ዓለም እየተዘዋወሩ ወንጌልን በማስተማራቸው ምክንያት ክርስትና እየተስፋፋ ስለመጣ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐሙ አስፈላጊ ሆነ (ማቴ፤ 28:19-20፣ መዝ፤18:4 ፣ ሐዋ፤1:8፣ ሮሜ፤14:18):: ስለዚህም በእንግሊዝኛ በ1611 (KJV) ፣ በአማርኛ በ1831፣ በትግርኛ እና በኦሮምኛ በ1900 (?) ተተርጉሟል::

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ከ 2100 በላይ በሚሆኑ የዓለም ቋንቋዎች፣ በሀገራችን በኢትዮጵያም ከ 30 በላይ በሚሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ይገኛል:: በኅትመት ብዛትም ሆነ በሥርጭት መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ቀዳሚውን ሥፍራ ይዞ ይገኛል።

## 4. የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት የሚረጋገጥባቸው ሁለት ዋና ዋና መንገዶች አሉ:: እነርሱም፦ በቃሉ ምንጭና ባለቤት በእግዚአብሔር የተሰጠው መለኮታዊ/አምላካዊ ማረጋገጫ (Divine Authorship) እና በሰዎች ማኅበራዊና ታሪካዊ ሂደት የታየ ማረጋገጫ (Human Authorship) ናቸው።

### 4.1. መለኮታዊ ማረጋገጫ (Divine Authorship)

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ 4600 ዓመት በሚጠጋ ጊዜ፣ ከ40 በማያነሱ ጸሐፍያን በተለያየ መልክአ-ምድራዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች የተጻፈ፤ እጅግ ብዙ በሆኑ መተርጉማን የተተረጎመ ቢሆንም የይዘት አንድነቱ ተጠብቆ መቆየቱ፤ በተለይም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል ያለው ምሥጢራዊ አንድነት መጽሐፉ ልዩ፣ ከእግዚአብሔር የተገኘ፤ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን ያረጋግጣል (ማቴ፤5:17፤ 22:34-40)::

ቃሉን በእምነት ሆነው በጸሎትና በምስጋና ሲናገሩት፣ ሲደግሙትና ሲዘምሩት እጅግ ኃይልን ከማድረጉ የተነሳ ደዌያትን የመፈወስ፣ አጋንንትን የማራቅ ምልክትን የሚያሳይ፣ በዘመናት ብዛት የማያረጅ፤ ይልቁንም ሕይወትን የሚያድስና የሚቀድስ መሆኑ ሁለተኛው ማረጋገጫ ነው (ዕብ፤4:11-13) ::

ሦስተኛው ማረጋገጫ ትንቢታዊ ምስክርነቱ ነው:: በቅዱሳን ነቢያት ***<u>"ይሆናል! ይደረጋል!"</u>*** ተብሎ ከብዙ ሺህ ዘመናት በፊት የተነገረው (የተጻፈው) ትንቢት የዘመን ርዝመት ሳይለውጠው ነቢያቱ በተናገሩለት ***<u>ዘመን፣ ቦታና ሁኔታ</u>*** መፈጸሙ ነው:: ለምሳሌም፦ የክርስቶስ የልደቱ ሥፍራ (ሚክ፤5:2)፣ የተወለደበት ቀን (ዳን፤9:25)፣ ከድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና

ስለመወለዱ (ኢ.ሳ፤7:14)፤ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመግባቱ (ዘካ፤ 9:9-10)፣ ስለ ስቅለቱ፣ ህማሙ፣ ሞቱና መቃብሩ (ዘካ፤12:10፣ መዝ፤21:16፣ ኢ.ሳ፤53:1-9)፤ ስለ ትንሣኤውና ዕርገቱ (መዝ፤77፥12፤ 46፥5) የተነገረው ትንቢትና የተፈጸመው ድርጊት ማረጋገጫ ነው።

አራተኛው ማረጋገጫ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የጥፋት ዘመናትን አልፎ ጸንቶ መገኘቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ አጥብቀው የተቃወሙ፤ የሕየወትን ራስ በቅንዓት እስከመስቀል ያደረሱ አይሁድ በተንኮል አስርገው ያስገቧቸው የሐሰት ክታባት (መጻሕፍት) ማዕበል ሆነው ያላሰጠሙት፤ ሮማውያን መጠን በሌለው አረመኔነትና ጭካኔ የመዘዙበት ሠይፍ ፣ ያነደዱበት እሳት በቀላሉ አቃጥሎና ቆነጣጥሎ ያላጠፋው የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጠበት ልዩ መጽሐፍ ነው::

## 4.2. ሰብአዊ ማረጋገጫ (Human Authorship)

ስለመጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት እግዚአብሔር በመለኮታዊ ጥበቡ በሰው ልቡና ከሚያሳድረው ቅዱስ እምነትና ለመጽሐፉ ከሰጠው ልዩ ኃይል በተጨማሪ በሰው ልጆች ታሪካዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሕይወት ውስጥ የተገለጠ እውነት መሆኑ ቋሚ ማረጋገጫ ነው::

***የከርሰ-ምድር (Archaeology) ጥናት*** - የከርሰ-ምድር ምርምር ግኝቶች የሰው ልጆች ያለፈ ታሪካቸውን እውነትነት ለማረጋገጥ በሰፊው ጥቅም ላይ ውለዋል:: የመጽሐፍ ቅዱስን ህላዌና ታሪካዊነት በእምነት ለመቀበል የሚቸገሩትን ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች በቁፋሮ የተገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅሪቶችን ምስክር በማድረግ ተአማኒነቱን ለማረጋገጥ ተችሏል::

***የሥነ ጽሑፍ የይዘት ተመሳሳይነት-*** መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናት ብዛትና በሁኔታዎች መለዋወጥ መካከል የይዘት አንድነቱ ተጠብቆ ኖሯል:: ይኸውም ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ኋለኛው ዘመን ድረስ በእስያ፣ በአፍሪቃ (ጥንታዊት ኢትዮጵያን ጨምሮ) እና በአውሮጳ ልዩ ልዩ ሥፍራዎች በሙሉም ሆነ በከፊል የተገኙ መጻሕፍቱ ፍፁም የይዘት አንድነታቸውን ጠብቀው ስለተገኙ የመጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነት ያረጋግጣል::

## 5. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ይሰጣል:: የእግዚአብሔር ሰው፣ ፍፁምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ይረዳል:: ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፤ በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል:: (2 ጢሞ፤ 3፣14-16)፤ ፍጹም ተስፋ ለሚገኝበት መጽናናትና በሃይማኖት ለመጽናት ያግዛል:: (ሮሜ፤ 15፣4)

ለሰማያዊና መንፈሳዊ ሕይወት ከሚሰጠው ልዩ ጥቅም በተጨማሪ ለምድራዊ ሕይወት መጠበቅና ለተሻለ ኑሮ የሚረዳ የዕውቀትና የሥልጣኔ ምንጭ ነው። በዚህም ረገድ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው የዕለት ከዕለት ሕይወት ውስጥ የማይዳስሰው ክፍል የለም። ለምሳሌም በግብርና (ኢ.ሳ፤5: 1-10፣ ሉቃ፤ 13: 6-9፣ ዘጸ፤23:10 ፣ ዘፍ፤ 41:25-36)፣ በምህንድስና (ዘፍ፤ 6:14-16)፣ በሕክምና (ኢ.ሳ፤ 38:21፣ ሉቃ፤ 10:34)፣ አስተዳደር (ዘጸ፤24:1፣ ዳን፤ 6:1-3)፣ ፍትሕ/ዳኝነት (1ነገ፤3:16-28፣ ዮሐ፤8:1-11) ለሰው ልጆች ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ሕይወት መቃናት የሚረዳ ፍጹም ዕውቀት የሚገኝበት ልዩ መጽሐፍ ነው።

"ወስብሐት ለእግዚአብሔር"

ይቆየን !

በዲ/ን አባተ፡ ጉበና
ሰኔ 1999 ዓ.ም.
ለንደን፤ ብሪታንያ።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ግናች

## ክፍል 1

(ትርጉም፣ ምንጭ፣ አጻጻፍ፣ ተአማኒነትና ጥቅም)



## 6. ትውፊትና የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና

### 6.1. ትውፊት

ትውፊት የሚለው ቃል ***“አወፈየ”* = *ሰጠ (አቀበለ)*** ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ***ቅብብል*** ማለት ነው። ይኸውም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ አበው ለውሉድ፤ ፊተኞች ለኋለኞች በቃልም ሆነ በጽሑፍ የሚያስተላልፉት የእምነትና የባህል ሥርዓት ነው።

ክርስቲያናዊ ትውፊት (Christian Tradition) በብሉይ ኪዳን ከአበው ወደ መሳፍንት፣ ከመሳፍንት ወደ ነገሥት፣ ከነገሥት ወደ ነቢያት ሲተላለፍ ቆይቶ ኋላም በሐዲስ ኪዳን በጌታችን በኢየሲስ ክርስቶስ ትምህርት የተገለጠ፤ ከክርስቶስ ወደ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት ወደ ሐዋርያውያን አባቶች እና ወደ ተከታዮቻቸው ሰማዕታት ከዚያም ለሊቃውንት ***በአፍ*** (Oral) ***እና በመጽሐፍ*** (Writen) እየተሸጋገረ ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዘመናችንም የደረሰ የክርስትና ትምህርት ነው።

ክርስቲያናዊ ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በኒቅያ(325)፣ ቁስጥንጥንያ(381)፣ ኤፌሶን (341) የተደረጉ ዓለም-አቀፍ (Ecumenical) ጉባኤያት ያሳለፏቸው የሃየማኖት ውሳኔዎች፣ መስቀል፣ ቅዱሳት ሥዕላት፣ ንዋያተ-ቅድሳት እና የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላል። ክርስቲያናዊ ትውፊት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በዘመናት ሁሉ ሳያቋርጥ በቤተክርስቲያን ላይ አድሮ ሲሠራ የመኖሩ፤ እንዲሁም ወደፊት እስከ ዓለም ፍጻሜ ሲሠራ እንደሚኖር ምስክር ነው። ከዚህም የተነሳ የተቀደሰ ትውፊት (Holy Tradition) ተብሎ ይጠራል።

በክርስቲያናዊ ትውፊት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ትልቁን ሥፍራ ይይዛል። ነገር ግን የሃይማኖት ትምህርት ብቸኛ ምንጭ አይደለም። (ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ የተነሱ ተቃዋሚወች (Protestants) መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ የሃየማኖት መሠረት ነው በሚል አመለካከት ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር (Sola Scriptora/Scripture Alone) ሌሎችን ማስረጃዎች አንቀበልም ይላሉ። ነገር ግን መሠረታዊ የሆኑ የሃየማኖት ምሥጢራትን (ለምሳሌ ምሥጢረ-ሥላሴ፣ የክርስቶስንና የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት እና የመሳሰሉትን) አብያተ ክርስቲያናት በአንድነት የተቀበሉት በዓለም-አቀፍ (Ecumenical) ጉባኤያት ላይ በተሰጠው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጎ በተቀነባበረው የማያሻማ ትምህርት ነው)። ሌላው ቀርቶ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው አሁን ባለበት ሁኔታ በጥራዝ መልክ ከማውጫ ጋር የተላለፈ ሳይሆን እያንዳንዱ መጻሕፍት በቅዱስ ትውፊት በቃልና በጽሑፍ ከወረደው ትምህርተ ክርስትና አንጻር ቁጥራቸው በቀኖና ተደንግጎ ነው። በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ያልነበሩ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ***የእግዚአብሔር ቃል፤ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ*** ብለን ያለጥርጥር ለመቀበል የቻልነው ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ ከመጣው መጽሐፍ ቅዱስን የማመንና የማክበር ትውፊት የተነሳ ነው።

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከ50-100 ዓ.ም. ባለው ጊዜ እንደተጻፉ ይታመናል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ባልተጻፈባቸው፤ ተጽፈውም በመላው ዓለም ባልተሰራጩባቸው ዘመናት የቤተክርስቲያን ሕይወት ተጠብቆ የኖረው በዘመናት ሁሉ ሳያቋርጥ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲሠራ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከክርስቶስ ወደ ሐዋርያት በቅብብል በወረደው ያልተጻፈ፤ የቃል (Oral) ትውፊትና ትምህርት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ከማይጠቅሙ ከንቱ ልማዶች በቀር የአይሁድን ትውፊት ያለነቀፋ ያከብር ነበር (ማቴ፤26:17-19፣ ዮሐ፤4:9)። ቅዱሳን ሐዋርያትም ከብሉይ ኪዳን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ትውፊት ይጠብቁ ነበር (ሐዋ፤3:1-3፣ ሐዋ:15:21)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ክርስቲያኖች በቃልና በመጽሐፍ ያገኙትን ትውፊት እንዲጠብቁ ሁልጊዜ በመልዕክቱ ያሳስባቸው ነበር (1ቆሮ፤11:2፣ 2 ተሰ፤ 2:15፣ 2ተሰ፤ 3:6) )። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ ጳውሎስ ስማቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈ፣ ***ኢያኔስና ኢያንበሬስ*** የተባሉ ጠንቋዮችን ስማቸውን ጠቅሶ የጻፈው ከአይሁድ ትውፊት (የቃል ታሪክ/Oral Tradition) አግኝቶ ነው (2 ጢሞ፤ 3:8)።

### 6.2. የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና

ቀኖና ማለት ልክ፣ ሰፍር፣ መጠን፣ ውሳኔ ማለት ነው። ይኸውም በቤተክርስቲያን የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ የሚወሰኑበት፣ የሚሰፈሩበት መለኪያ ማለት ነው። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ እስከ ዕርገቱ ድረስ ለቅዱሳን ሐዋርያት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት (ቤተክርስቲያን) የነገራቸው፤ ሐዋርያትም ጽፈው የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ቀኖና (ሥርዓት) እንደሆነ ተገልጿል (ሐዋ፤ 1:1-4)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖናም በቤተክርስቲያን የሚነበቡ፤ ለትምህርት፣ ለተግሣጽ፤ ልብንም ለማቅናት የሚጠቅሙ፤ ክርስቶስን በማመን መዳን (ሕይወት) የሚገኝበትን ጥበብ የሚሰጡ መጻሕፍት ተለይተው የተወሰኑበት ሥርዓት ነው።

#### *ሀ). የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቀኖና*

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቀኖና መነሻ የዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁሉም አብያተክርስቲያናት ያለልዩነት የሚቀበሉት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ አይሁድ (ዕብራውያን) የሚቀበሉትን ባለ 24 (39) ቢሆንም አይሁድ በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ዝርዝር ያላካተቷቸው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍትነት የተቀበለቻቸው ሌሎች መጻሕፍትን ጨምሮ 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን እንቀበላለን።

#### *ለ). የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቀኖና*

በሐዲስ ኪዳን ዘመን ቤተክርስቲያን እየሰፋች በሄደችበት ወቅት በተለይም በ 1ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን አይሁድ ክርስትናን ለማጥፋት ከሞከሯቸው ብዙ ዘዴዎች አንዱ መንፈሳውያት (አምላካውያት) ያልሆኑ የሐሰት ክታባትን (መጻሕፍትን) በንጹሐን ሐዋርያት ስም እየጻፉና እያባዙ ወደ ቤተክርስቲያን አስርጎ በማስገባት የክርስትናንና የቅዱሳት መጻሕፍትን ተአማኒነት ማጉደፍ ነበር።

በዚህም መሠረት ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሐሰት ክታባት ለመለየት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ብዙ ቅዱሳን ሐዋርያትና ሐዋርያውያን አባቶች (Apostolic Fathers) ቀኖና ሠርተዋል እንዲሁም የተለያዩ ጉባኤያት ተካሂደው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ብዛትና ዓይነት በቀኖና ተወስኗል።

ከነዚህም ቀኖና አበው እና ጉባኤያት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

❖ <u>ቀኖና ሐዋርያት (ሲኖዶስ)</u>

የመጀመሪያው የሐዋርያት ሲኖዶስ የተካሄደው በ50 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ነው (ሐዋ፤ 15:17-20)። ቅዱሳን ሐዋርያትም በዚህ ሲኖዶሳቸው 85 አንቀጾችን የያዘ ቀኖና (ሥርዓተ-ቤተክርስቲያን) ደንግገዋል። የዚህ ውሳኔ 85ኛው አንቀጽ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ብዛትና ዝርዝር የተወሰነ ሲሆን ዝርዝሩም ሁሉንም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና 35 የሓዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ያካተተ ነው።

❖ <u>ጦማር ዘቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ</u>

ቅዱስ አትናቴዎስ በ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእስክንድርያ የተነሣ፤ የኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ጠበቃ (Defender of Orthodoxy) በመባል የሚታወቅ ታላቅ አባት ነው። በዚህ ዘመን እስክንድርያ በከፍተኛ የክርስትና ትምህርት ማዕከልነቷ እጅግ የገነነችበት ዘመን ስለነበረ የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት አጽዋማትን፣ በዓላትንና ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ለሌላው ክርስቲያን ዓለም የማወጅ ሥልጣን ነበራቸው።

ስለሆነም ቅዱስ አትናቴዎስ በ349 ዓ.ም. የዓመቱን በዓላትና የዓቢይ ጾምን መጀመሪያ ባወጀበት መልዕክቱ (Circular) የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ብዛትና ዝርዝር አብሮ አስታውቋል። እንደ ቅዱስ አትናቴዎስ አገላለጽ መጽሐፍ ቅዱስ ሚያካትታቸው መጻሕፍት መላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍተና 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ነው።

❖ <u>ቀኖና ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ</u>

ቅዱስ ጎርጎርዮስ (329-389) በቅዱስ አትናቴዎስ ዘመን የተነሣ ታላቅ ሐዋርያዊ አባት ነው። በሌላ አጠራር ጎርጎርዮስ ታላቁ (The Great)፣ ገባሬ መንክራት (Miracle Maker)፣ ነባቤ መለኮት (Theologian) በመባልም ይታወቃል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከጻፋቸው መጻሕፍት መካከል ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት በተናገረበት ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን ዝርዝር ያመለከተበት ይገኛል። ዝርዝሩም ከቅዱስ አትናቴዎስ ጋር ይመሳሰላል።

❖ <u>የሎዶቅያ ጉባኤ (363 ዓ.ም.)</u>

ከላይ በተከታታይ እንደተገለጠው ቅዱሳን ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ሐዋርያውያን አባቶች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ካስተላለፉልን ውሳኔ በተጨማሪ ብፁአን አባቶች በተለያየ ጊዜ ተሰብስበው ያሳለፏቸው የሃይማኖትና የቀኖና ውሳኔዎችም ምስክር ናቸው:: የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን በተመለከተ ውሳኔ ከተላለፈባቸው ጉባኤያት መካከል በ363 ዓ.ም. ሎዶቅያ በተባለች ሀገር የተካሄደው ጉባኤ ነው።

በዚህም ጉባኤ የተገኙ አባቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ለጸሎትና ለትምህርት የሚነበቡ መጻሕፍት በቀኖና ቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ወስነዋል:: በተለይም በአንቀጽ 59 እና 60 ላይ የሚነበቡ የሐዲስና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ተቀምጠዋል።

❖ <u>የሒፖ ጉባኤ (393)</u>

አሁን በመላው አብያተክርስቲያናት ተቀባይት ያገኘውን የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ቀኖና ለመጀመሪያ ጊዜ በምልዓት የተቀበለው ጉባኤ የሒፖ ሲኖዶስ (the Synod of Hippo Regius) ነው። የዚህ ጉባኤ ውሳኔ በጽሑፍ ያልተገኘ ቢሆንም አሁን ከዚህ ቀጥለን በምናየው የቀርጠግና (Carthage/Carthagina) ጉባኤ ውሳኔ ላይ ተጠቅሶ ተገኝቷል::

❖ <u>ሦስተኛው የቀርጠግና ጉባኤ (397)</u>

ከላይ እንደጠቀስናቸው ጉባኤያት ሁሉ ይህ 3ኛው የቀርጠግና ጉባኤ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ተብለው በቤተክርስቲያን ለአገልግሎት የሚነበቡ መጻሕፍትን ዝርዝር ካጸደቀ በኋላ፤ የጻድቃን፣ የሰማዕታት ድርሳን እና ገድል በየበዓላቱ እንዲነበቡላቸው ወስኗል።

**“ወስብሐት ለእግዚአብሔር”**

ዲ/ን አባተ ጉበና
ሐምሌ 1999 ዓ.ም.
ለንደን፤ ብሪታንያ።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጉዳይ

## ክፍል 2

(የመጽሐፍ ቅዱስ ትውፊትና ቀኖና)

